Association of Ethiopians in Europe

info@ethiodiaspora.net www.ethiodiaspora.net

ግንቦት 5 ቀን 2013 ዓመተ ምህረት

# ይድረስ ለኢትዮጵያ መንግስት

P.O.Box: 1031
Addis Ababa, Ethiopia
Lorenzo Te`azaz Street
Tel: +251 111 400 740
Fax: +251 111 226 292
Email: info@pmo.gov.et

## ከኢትዮጵያዉያን ማህበር በአውሮፓ የተሰጠ መግለጫ!

አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ

ጉዳዩ; የኢትዮጵያ መንግስት በሚያዝያ 27 ቀን 2013 ዓመተ ምህረት የሽብር ተግባር ሲያቀናብሩ ደርሽባቸዋለሁ በሚል ስማቸውን ዘርዝሮ የጠቀሳቸውን ግለሰቦች ሲፈፅሙ ነበር ብሎ ከዘረዘራቸው ውንጀላዎች ውስጥ የሚከተሉት ከታች ሰፍረዋል;-

ምርጫ ለማደናቀፍ ሁከት ለመፍጥር መሞከር፣

እኛ የሀገራችን የኢትዮጵያ ጉዳይ ግድ የሚለን፣ በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ነዋሪ የሆንን ኢትዮጵያውያን 'በአውሮፓ የኢትዮጵያውያን ማሕበር'' በሚል ሕጋዊ እውቅና ባለው ጥላ ስር ተሰባሰበናል። የማህበሩ አባላት ከአሜሪካ ከካናዳ ከአፍሪካ ወዘተ የተዉጣጡ ናቸው:: አባሎቻችን በየሚኖሩባቸው ሀገራት በተለያዩ ዘርፎች ለኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። የሀገራችንን ጉዳይ በንቃት እየተከታተልን የምንኖርባቸው ሀገራት የውጪ ግንኙነት ተጠሪዎች ሙሉ መረጃው እንዲኖራቸው በማድረግም ላይ እንገኛለን።

የፖለቲካ ድርጅት አይደለንም: አባላቱ የተለያየ አቋአም ያላቸው ናቸው:: እንዲያዉም ለአብነት ያህል የኢዜማ የአብን የብልፅግና የባልደራስ ወዘተ የመንግስት ደጋፊዎች የኤምባሲ ሰዎችም አሉበት:: ስለዚህ የምናካሄደው የምስጢር ሥራ ምንም የለም::

ስራችን ዉይይታችን ሁሉም እዚያው ግሩፕ ዉስጥ ወይም ገፃችን ላይ ይታተማል::
በክሱ ላይ የተጠቀሱት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉትን ግለሰቦች ስማቸዉንም ሰምተን አናውቅም::
ክሱ ምንም አይነት መረጃ ሳይኖረው መመሰረቱ የተወሰኑ ግለሰቦች የአባታቸው ስም እንኳን

ያለመጠቀሱ ነው::
መሰረት በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለንም::

በማኅበራችን አባላት ላይ የሀሰት ውንጀላ፣ የስም ማጥፋት ዘመቻ የተከፈተብንን ጭምር ስንሰማ;- ከፍተኛ ሀዘን፣ ቁጭትና ቁጣ ፈጥሮብናል። ምክንያቱም ፣ ይህ የሀሰት ውንጀላ፣ ስም ማጥፋት ዘመቻ:- ለህዝብ አብሮነትና እኩልነት ስለማይረባ፣የማንኛውንም ሰብአዊ ፍጡር በነፃ ና ያለ ተጽዕኖ ሀሳቡን በልዩ ልዩ መንገድ የመግለፅ፣ መናገር፣ መፃፍ፣ ማሰብና በሰላማዊ ሰልፍ በስነ ጥበብ፣ በሀዘን፣ በደስታ፣ ማስተላለፍና ከሌላ ወገን ሀሳብ መቀበልም፣ ከእግዚአብሔር ከፈጣሪያችን የተሰጠን መብቶች ስለሆኑ የማንንም ፈቃድ ሳንጠይቅ ማንሸራሸር እንችላለን።

ይህንን በአለም ህግ በተለይ በአርቲክል 19 የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን 1966 ለሁሉም ሰው የተደነገገውን መብታችንን ማፈን በራሱ በህግ ክልክል ነው።

(Article 19 the International Convention on Civil and Political Rights 1966.; Article 19 UDHR 1948).

የአለም አቀፍ ህጎችን በተለይ የመንግስት ቀዳሚና ዋና ተግባሮቹን የዜጎችን በህይወት የመኖር ጥበቃና የደህንነት ዋስትና ሀላፊነቱን እንዲወጣ፣ የደነገገውን የተባበሩት መንግስታት ውል ወይም ቻርተር የጣሰና የህዝብን እልቂት ያላስቆመ በመሆኑና ይህንን የሰብዓዊ ና ህጋዊ መብት እንዲከበር መጠየቅ, ዜጎችን አትግደል, አታፈናቅል ብለን መጠየቅ ያስመሰግነናል እንጂ ልንወነጀል አይገባንም።

የኛ ማህበር ዉስጥ ከ 300 መቶ ያነሱ አባላት ያሉት ነው:: ሌላው ከ1ሺ በላይ ያለው በቴሌግራም ካናል ስለ አዲስ አበባ ዝም አንልም ስለሚለው ግሩፕ የሰማነውም ከናንተ ነው:: ስለዚህ ግሩፕ ማህበራችን የሚያውቀው ነገር የለም:: እያንዳንዱን ግለሰብ ጠይቃችሁ ማጣራት የናንተ ሥራ ነው::

ያሁሉ ኢትዮጵያዊ ሻሸመኔ አጣዬ ወለጋ ወይም ቤንሻንጉል ላይ ሲጨፈጨፉ ሲታረዱ ያላየ: የዚያን አካባቢ አስተዳዳሪዎችና የፖሊስ ኃላፊዎች እንኳን ጠርቶ ያልጠየቀ ወይም ለህግ ያላቀረበ ሱዳን ሃገራችንን መሬታችንን ስትወር ያልሰማ የድህንነት ድርጅት እንዴት ነው አውሮፓና አሜሪካ ድረስ ሄዶ እንዲህ አይነት ወንጀለኛ አገኘሁ ማለት የቻለው?

ስማቸው ክሱ ላይ የሌለ ኢትዮጵያዉያን ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ ሁሉ በጣም አዝነው ደንግጠዋል:: በማህበራዊ ሚድያ ላይ እኛን ደግፈው ተናግረዋል ፅፈዋል :: ጭራሽ ዉጭ ያለው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እኛም አብረን ተፈርጀናል ብለው ፈርተው ወደ ሃገራቸው እንዳይመለሱ፣ ኢንቬስት እንዳያደርጉ እርዳታ እንዳይሰጡ እየገፋፋችሁ ነው::

የወገኖቻችንን ብቻ ሳይሆን የማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር ዘር ማጥፋት, ፍትህ መጓደልና የመሳሰሉትን ጥሰትና ወንጀሎች በየትም አለም ቢፈፀሙ እናወግዛለን፣ እንዲቆሙም ከተበዳዮች ጎን ምንግዜም እንቆማለን።

መንግስት የህዝቡን ደህንነትና ቤትና ንብረቱን መጠበቅ ዋና ቁልፍ ሀላፊነትና ግዴታው ነው።

መንግስት የሚከተሉት የሰብአዊ ና ህጋዊ መብቶችን ባለማክበሩና ተጥሰው ዜጎች በየቀኑ እየተገደሉና ከመኖሪያቸው እየተፈናቀሉ ነው።

ከእነዚህም ውስጥ ከዚህ በታች ያሉት ናቸው;-

“ Such as, Universal Declaration of Human rights 1948, Uns Convention on Political and Civil rights 1966”; Prohibition, Prevention and Punishment the Crime agains Genocide 1948.

ስለሆነም ይህ ያለምንም ማስረጃ የቀረበ መሰረተቢስ ክስ፣ ውንጀላና ሰብአዊና ህጋዊ መብታችንን የጣሰ ነው።

ዘርፈ ብዙ ጀኖሳይድ እየተፈፀመበት፣ እየተፈናቀለና መሮቱ፣ ቤትና ንብረቱ ሲወድምመት ይህንን ወንጀል ማውገዝ፣ ማጋለጥትና ማስቆም ኢትዮጵያውያን ብቻ ስለሆንን ሳይሆን ይህ የአለምን ህዝብ ሁሉ የሚመለከት ስለሆነ ነው።

ሌላው ጉዳይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ቤትና በማስረጃ ወንጀለኛ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ከወንጀል ነፃ ሰው ሆኖ መወሰድ ይገባዋል የሚለውን አለም አቀፍ ሰብአዊና ህጋዊ መብታችንን የጣሰም ስለሆነ አጥብቀን እናወግዘዋለን።

Article 14 International Convention on Civil and Political rights 1966, provides that, “Everyone has a right to be presumed innocent until proven guilty, and has equal right before the law...” .

ከሁሉም በተለይ በኛ ስም ተፈጥሯዊ ፣ ሰብአዊ ና ህጋዊ መብታቸውን በሰላማዊ ሰልፍም ይሁን በፅሁ የሚጠይቁ ንፁህን ዜጎችን በተለይ አማራ ዘር የሆኑትን በእምነታቸው ጭምር እየለዩ ማሰርና ማዳከም በትልቁ አስቆጥቶናል።

ይህ ዘመቻ በአማራ ዘር ላይ የሚደረገውን ዘርፈ ብዙ የዘር ማጥፋት ወንጀልና ማፈናቀል እንዳናጋልጥ እኛን ለማስፈራራት፣ ለማሸማቀቅ የተሴረ ሴራና ዘመቻ ነው ብለን እንድናምን ተገደናል፣ በጣም አሳዝኖናል አስቆጥቶናልም።

በተጨማሪም በዚህ መሰረተቢስ የሀሰት ውንጀላ ከአለም አቀፉ የፖሊስ ድርጅት( INTERPOL ) ጋር ማያያዙ አሳሳቢ ነው።

የኢንተርፖል ህግና ስልጣን የደነገገውና ወንጀለኛን አድኖ እንዲይዝና አሳልፎ እንዲሰጠው ቢያስፈልገው እንኳ በዘር ማጥፋት የሚፈለጉትን የተፈረደባቸዉን ሰዎች እንጂ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን መያዝ አይመለከትም።

ወንጀለኞች ያሉትም እዚያው አገራችን ኢትዮጵያ ነው፣ ያውም ህፃናት እርደው የሚፎክሩ ጭምር ናቸው ።

ለመጠቆም ያህል የኢንተር ፖል ተግባሩ, የተሰወሩ አሸባሪዎችና ጀኖሳይድ ወንጀል፣ በሰብአዊ ፍጡር ጭፍጨፋ የፈፀሙ፣ በተለይ በተኙበት ህፃንና ሴት፣ አቅመ ደካሞችን የሚያርድ ቡድን፣ በጥቅሉ በአገር ውስጥና ውጭ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ወንጀል ተብለው የተከለከሉ ወንጀሎችን ለፈፀሙ ወንጀለኞች ነው እንጂ፣ እኛን አይመለከትም።

(“Mis use and abuse of INTERPOL usually is practiced by authoritarian regimes by weaponizing INTERPOL Red Notice system, to silence political oponents based abroad, who are standing against human rights violations in their home country and beyond “.

ስለዚህ  የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽንና የኢንፎርሜሽን መረብና ደህንነት ስም የወጣው ክስ ደረጃዉን ያልጠበቀ ተራ ዉንጀላ መሆኑ ያስታዉቃል:: ይህም የኢት

ዮጵያን ህዝብ መናቅና አሳሳቢም ነው።

የኛ የቆምንለት ዋና አላማ የህዝባችን በጋራ፣ በኩልነት፣ በፍትህ፣የሁሉም መብት ተከብሮለት በፍቅር እንዲኖር ብቻና ብቻ ነው። የማህበሩ አባላት በተከፈተው የዋትስአፕ መድረክ ፣ሀሳባችንን በነፃነት በድምፅ፣ በፅሑፍና በዙም ጭምር እንለዋወጣለን፣ እንወያያለን።

ነገርግን ማህበሩ ከተቋቋመበት አላማ ውጭ በማንኛውም በሀሰትና በተዛባ ወንጀል ተብሎ በተለጠፈብን ወንጀሎች አልተሳተፍንም። ማንኛውንም ወንጀል የምንኮንን ነን።

ይህ መድረክ የተመሰረተበት አላማ በዋናነት፣- የኢትዮጵያን ህዝባችንን የሰብአዊ ፣ ተፈጥሯዊ፣ ዲሞክራሲዊና የመልማትና ከድህነት በፍጥነት እሚላቀቅበትን ለመምከርና ለማገዝም ነው።

ስለሆነም አሁን ያለው መንግስት እኩል ልማትና መልካም አስተዳደር፣ የህግ የበላይነት በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች፣ ዘርና፣ ጎሳ ሳይለይ  እንዲያስከብር፣

የአባይ ግድብን የመሳሰሉ አገራዊ የልማት ግንባታዎችን ሁሉ በገንዘባችን፣ በእውቀታችንና በቴክኖሎጅ ጭምር ለመደገፍ ነው። እስካሁንም በተቻለን አቅም ለአባይ ግድብም ፣ ለተፈናቀሉና ሜዳ ለወደቁ ወገኖቻችን፣ ለመከላከያ ሰራዊታችን፣ በኮሮና ወረርሽኝ እርዳታ አድርገናል።

መንግስት መልካም ሲሰራ እናወድሳለን፣ የዜጎችን መብት ሲጥስ እንኮንናለን። ይህ ደግሞ ሰብአዊ ግዴታችንና መብታችን ነው።

ከሰራናቸው ተግባሮች በጥቂቱ:

1-ፕረዚዳንት ትራምፕ የአባይ ግድብን በተመለከተ በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉትን ዛቻ በመቃወም ዉሳኔ አስተላልፈን ለአሜሪካ መንግስት ደብዳቤ አስተላልፈናል::

2-በሀገራችን የተከሰተዉን የኮሮና ወረርስኚኝ በሽታ ለመካለከል በያለንበት እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ልከናል::

3-መከላከያ ሰራዊታችን በትግራይ ለሚያደርገው የሕግ ማስከበር ዘመቻ መዋጮ  አበርክተናል::

4-የአዉሮፓ ህብረት በኢትዮጵያ ላይ ለማደረግ የተነሳዉን የኢኮኖሚ  አቀባ በመቃወም (March 11, 2021) ብራስልስ ቤልጂየም ድረስ በመሄድ የተቃውሞ ሰልፍ አድርገናል !

እኛ ፍላጎታችን ኢትዮጵያን ማተራመስ ሳይሆን ከሁሉም በፊት አገራችን ዉስጥ ሰላም እንዲሰፍን ነው:: ብዙዎቻችን ሀገራቹን በሰላም የዲሞክራሲ ስርዓት እንዲሰፍን የታገልን በወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ጊዜያት የተከሰስን ነን:: እኛ ሽልማት እንጂ ክስ አይገባንም::

ኢትዮጵያ ዉስጥ በእርግጥ እጅ ከፍንጅ ተያዙ የተባሉት ግለሰቦች ከማህበሩ ጋራ ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ስለሆነ የተያዘባቸው ማስረጃ ካለ እዚያው አነሱን መጠየቅ እንጂ ከኛ ማህበር ወይም ከአባላት ጋር ማያያዝ ተገቢ አይደለም:: የሚያያዝ ከሆነም ማስረጃዉን በዝርዝር እንድታቀርቡልን::

የኛ ማህበር እንዲያዉም በሀገራችን ምርጫ እንዲካሄድ የሚደግፍ እንጂ ምርጫ እንዳይደረግ የሚል ዘመቻ አድርጎ አያዉቅም:: በዚህም የተነሳ ወረቀት በትኖ አያውቅም:: ገንዘብም ልከን አናውቅም:: በራሪ ወረቀት የበቱነትን አዚያው ራሳቸዉን መጠየቅ ነው ያለባችሁ::

ስለዚህ ለወነጀለን መንግስት የሚከተሉትን እንጠይቃለን;-

1. በሀሰት በህዝብ መገናኛ ቴሌቪዥን ላቀረበብን ክስ ስህተቱን አርሞ በአደባባይ በወነጀለበት ቴሌቪዥን ይቅርታ እንዲጠይቀን፣

2. ከኛ ጋር አጣምሮ ሰብአዊና ህጋዊ መብታቸውን በሰላማዊ መንገድ የጠየቁትን በተለያዩ የአገራችን አካባቢ ነዋሪዎችና የተለያዩ ፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ማንኛውም ዜጋ ማሰር፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶቻቸውን የጣሰ ከሆነ፣ ተጣርቶ ሊፈቱ ይገባቸዋል ብለን እንጠይቃለን።

3. በአማራው ህዝብ ላይ የሚፈፀመው ዘር ማጥፋት፣ ማፈናቀል፣ የአማራ የሰላም ታጋዮችን መግደል፣ ማሰር፣ ማዋከብ በአስቸኳይ እንዲቆምና የተፈናቀሉት ከይቅርታና ካሳ ጋር ወደነበሩበት መልሶ እንዲያቋቁማቸው፣

4. ለዚህ ሁሉ የህዝብ እልቂት፣ ድህነት፣ ዘላቂ ሰላምና እጦት መሰረታዊ ችግሩ፣ በዘርና ቋንቋ በዘረኛ አስተሳሰብ አገራችንን በክልል ከፋፍሎ ህውሀት የፈጠረውና ያለ ህዝብ ፈቃድና እውቅና ህዝብ ላይ የጫነው ሰነድ ስለሆነ መሰረዝና፣

5. የመንግስት ስልጣን የሚመነጨውና መንግሥት የሚፈጠረው በህዝብና ህዝብ ራሱ በፍቃዱ በሚያፀድቀው ላእላይ ህግ ወይም ኮንስትቲውሽን ስለሆነ፣ ህጋዊ ሁሉንም ኢትዮጵያንን ያሳተፈ አዲስ ህግ አርቃቂ ኮሚሽን እንዲቋቋምና እንዲረቅ፣ይህ አዲሱ ህግ በዶክተር አብይ ተፈርሞ ከፀደቀ በኋላ፣ ህዝቡን ለምርጫ ማዘጋጀትና
የራሳቸውን ፓርቲ ይዘው አንዱ ተወዳዳሪ የመፍትሄ አካል በመሆን ከተጓዝንበት አስከፊ አሮጌ ስርአት ወደ ዲሞክራሲ ሽግግር እንዲወስዱን መጠቆም እንወዳለን።

   ይህን ማሳሰቢያ የመፍትሄ ሀሳብ የምናቀርበው ለወገናችን ከልብ ስለምናስብና ከፍተኛ ስጋት ስላለን፣ የሚበጀውን ለመጠቆም ነው።

   በአማራና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ጀኖሳይድ እየተፈፀመ ስለሆነ እንጂ፣ በምንም መልኩ የልመና፣ የፍራቻ፣ ወይም የዛቻ፣ የስልጣንም ፍላጎት የለንም።

   ስልጣንና እንደጤዛ የሚረግፍ ጥቅም ብንፈልግ፣ የሚጨፈጨፉት ንጹሀንን ከምንም አንቆጥራቸውም ነበር። በየአደባባይ ስቃያቸው እንዲቆም አንሟገትም አንቆምም ነበር።

   የህዝባችንን ጉዳት ዘግተን የሀሰት ወሬ ለቃቃሚ ተላላኪ ድኩማን እንሆን ነበር።

   ስለዚህ መንግስትንና ሁላችሁንም ደግመን የምናሳስባችሁ፣-ሁላችንም የኢትዮጵያ ልጆች ባለቤቶች ነንና ለአንዴ በዘመናችሁ፣ ይህንን የዘረኝነት አዙሪት ሻሩት።

በመሆኑም ይሄ በዉጭ ሀገር በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የተወሰደው የስም ማጥፋት ክስ ቶሎ እንዲነሳ እንጠይቃለን:: ያለበለዚያ በስም ማጥፋት ወንጀል በያለንበት ሀገር ሕጋዊ መፍትሄ ለመሻት እንገደዳለን::

ወገናችሁን ወደ አንድነቱ መልሱት መፍትሄው ይህ ብቻ ነው።
ወያኔ የከለለውን ግንብ አፍርሱት።
ደግሞም ትችላላችሁ፣
ህዝብም የበለጠ ከነቤተሰባችሁ ያከብራችኋል።
እኛም ከጎናችሁ እንቆማለን።
ይኸው ነው፣ ሌላ አጀንዳ የለንም !

ከአክብሮት ጋር
ከኢትዮጵያዉያን ማህበር በአውሮፓ
www.ethiodiaspora.net
e-mail: info@ethiodiaspora.net